# ኢሕአፓ በአትላንታ ከተማ ህዝባዊ ስብሰሰባ አደረገ።

ባለፈው ሳምንት ቅዳሜ June/9/2007 የኢሕአፓ ከፍተኛ አመራር አባላት ወደ አትላንታ ከተማ በመምጣት ሁለት ስብሰባወችን አድርገዋል። የመጀመሪያው ስብሰባ በአትላንታ አካባቢ የሚገኙ የኢሕአፓ አባላት ጋር የተደረገ ስብሰባ ሲሆን ሁለተኛው ስብሰባ ደግሞ በአትላንታ ነዋሪ ከሆኑ ኢትዮጵያዉያኖች ጋር የተደረገው ህዝባዊ ስብሰባ ነበር። በነኝህ ስብሰባዎች ላይ የተገኙት የኢሕአፓ ከፈተኛ አመራር አባላት አቶ ለይኩን ተሾመና ዶክተር ጌታቸው በጋሻው ሲሆኑ በህዝባዊው ስብሰባ ላይ ለተገኙት ተሳታፊዎች የኢሕአፓን የትግል ተመክሮ ተነስተው በአሁኑ ሰአት በአገራችን ሰላለው ጠቅላላ ሁናቴና ኢትዮጵያውያን ለፍትህና ለዴሞክራሲ የሚያደርጉት ትግል አቅጣጫው ምን መሆን አለበት በሚሉ አርእስት ላይ መንደርደሪያ በመስጠት የስብሰባዉን ተሳፊዎች ለማወያየት ችለዋል።

ስብሰባው አምስት ሰአታት የፈጀ ሲሆን። የኢሕአፓ አመራር አባላት ንግግራቸውን አጠር አጠር በማድረግ ብዙው ሰአት ለጥያቄዎችና ለአስተያየቶች በመስጠት ከተሳታፊዎችም ጠንከር ያሉ የበሰሉ አስተያያቶችና ጥያቄዎች ተሰንዝረዋል። ከነኝህም ጥያቄዎችና አስተያየቶች መካከል ኢሕአፓ በወጣቶች ዙሪያ የሚያደርገውን እንቅስቃሴና ከወጣቱ ትውልድ ጋር ያለውን ቅርርብ፣ ድርጅቱ ታክቲክና ስትራቴጂን እንዴት እንደሚመለከት፣ ከሌሎች ድርጅት አባላት ጋር ስለመቻቻል፣ በቅርቡ በአገራችን ስለሚደረገው የሺህ አመት ክብረ በአልን አስመልክቶ ድርጅቱ ማድረግ ሰለሚገባው እንቅስቃሴ፣ ኢሕአፓ የህብረት አባል ሆኖ እያለ ስብሰባ ለብቻው ስለመጥራቱ፣ የብሔራዊ እርቅን በተመለከተ መደረግ ሰለሚገባው ጥረት፣ በአሁኑ ሰአት የህብረት ግንባርን አንገብጋቢነትና ኢሕአፓም ሆነ ሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች ማድረግ ሰለሚገባቸው ጠንካራ ግንኙነትና ስምምነት እንዲሁም የወያኔን የመረጃ ማምታት (disinformation) ስለመቋቋም የሚሉት በአበይትነት የሚጠቀሱ ናቸው።

በስብሰባወ የተገኙት ተሳታፊዎች ካደረጉት ነቃ ያለ ተሳትፎ በተጨማሪ በስፍራው የተገኙት የኢሕአፓ አመራር አባላት አንድ ህዝብ ለነፃነቱ ያለውን ጥማት የሚለካው ከድርጅቶች ጋር ባለው ቅርርብና መመካከር መሆኑን አፅንኦት ሰጥተው፤ ለስብሰባው የተገኙትን አመስግነው ወደ ድርጅቶች ስብሰባ በመሄድ፣ በመሳተፍና በአባልነት በመግባት የድርጅቶችን የትግል አቅጣጫ ፈር ማስያዝ እንደሚገባ አስገንዝበዋል። ኢሕአፓም እንደ ድርጅት ሲታገል በኖረበት ኢትዮጵያዊነት አጥብቆ እንደሚፀና ቃል ገብተው በስብሰባው ለተገኙትን ውድ ኢትዮጵያውያን አድናቆታቸውንና ፍቅራቸውን ገልፀው በመሰናበት ስብሰባወ በጥሩ ሁኔታ ተጠናቋል።